የመላ ኢትዮጵያ ሶሽያሊስት ንቅናቄ

ታህሣሥ 19 ቀን 1990 ዓ.ም.

# በአመጽ ቢመጡብን በአመጽ

# በሰላም ቢመጡብን ደግሞ በአመጽ

ነባሩ የወያኔ ኢህአዴግ መፈክር ይህ እንደሆነ ስለምናውቅ ዛሬ በሶስተኛው የህወሃት / ኢህአዴግ ጉባኤ ላይ በታጠቁ ተቃዋሚ ኃይሎች በመጡበት መንገድ እንቋቋማቸዋለን ተብሎ የተገለጸው አቋም ምንም አላስደነቀንም።

ወያኔ/ኢህአዴግ አውቆ አላዋቂ ይመስላል እንጂ በትጥቅና በአመጽ ተነስተውብኛለና እፋለማቸዋለሁ የሚላቸው ኃይሎች በድንገት ከሰማይ የወረዱ ኃይሎች አይደሉም። ከኦነግ እስከ ኢአግ፣ ከአፋር እስከ ኦጋዴን ታጣቂዎች በትጥቅ ትግል የተሰማሩት ኢህአዴግ አስቀድሞ በመጣበት የትጥቅ ትግል ጎዳና እንመለከታለን ብለው የተነሱ ኃይሎች እንጂ ዲሞክራሲ ያውላችሁ፣ ሰላማዊ ትግል ይቻላል እየተባሉ በጦር ጠማሽነት ራሳቸውን ለመሰዋእትነት የዳረጉ ዜጎች አይደሉም።

ወያኔ ኢህአዴግ አውቆ አላዋቂ ይመስላል እንጂ ታጣቂዎቹ በመጡበት እመክታቸዋለሁ ሲል ዛቻው በነሱ ላይ ብቻ አይደለም። የተለያዩ ታጣቂ ኃይሎችን ለመዋጋት በሚያደርገው መፍጨርጨር ሳቢያ የነዚህ ኃይሎች ደጋፊዎች ናችሁ እያለ በገጠርም ሆነ በከተማ በምንም ዓይነት በትጥቅ ያልመጡበትን ሰላማዊ ዜጎች ማሰር፣ ማንገላታትና መረሸንን እቀጥላለሁ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ወያኔ ኢህአዴግ አለአግባብ ተጠቅቻለሁና ራሴን ለመከላከል በትጥቅ የመጡብኝን በትጥቅ እፋለማለሁ ሲል በብእር የመጡብኝ በብእር እቋቋማለሁ ማለቱ እንዳይደለ በጋዜጠኞች ላይ በየእለቱ የሚወርደው ግፍ ህያው ምስክር ነው። በሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞ እሰማለሁ ያለን ኃይል ለመቋቋም ደጋፊዎቼን እኔም ሰልፍ አወጣለሁ ማለቱ እንዳይደለ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ተኩስ ሲከፍት አይተነዋል። በሰላማዊ ዘዴ ህዝብን አደራጅቼ እፋለምሃለሁ የሚለኝን ዜጋ እኔ ህዝብን በይበልጥ አደራጅቼ በህዝብ ፊት በዲሞክራሲያዊ ዘዴ እዋጋዋለሁ ማለት እንዳልሆነ ሌሎች እንዳይደራጁ መሪዎችን ሲያስር፣ ሲያንገላታና ሲረሽን፣ የነጻን ምርጫ ጎዳና አሻፈረኝ ብሎ ሲዘጋ ያየነው ነው።

ባጭሩ ይህ አገዛዝ በመላ ህብረተሰቡ ላይ ጦርነት አውጆ በአመጽ ብቻ የሚገዛ ጸረ ህዝብ ኃይል ነው። ለዚህ አጸፋው የአንድ ወይም የሁለት የፖለቲካ ኃይሎች የተናጠል ትግል አይደለም። የትግሉን ግንባር ቀደምነት ሃላፊነት የተቀበሉ ኃይሎች ሁሉ አመጽ የተሰነዘረበት ህብረተሰብ በአነስተኛ የጋራ ዓላማ ሥር ተሰልፎ እንዲነሳ ዲሞክራሲያዊ የሆነ አማራጭ አቅርበው በጋራ መነሳት አለባቸው። ወያኔ ተቃዋሚ በሚላቸው ኃይሎች መሃከል ምንም ልዩነት አያሳይም። ማንኛውንም ዓይነት የትግል ስልት ለመቋቋም የሚፈልገው በአመጽ ነው። ዲሞክራሲያዊ አማራጭ ኃይሎችም የትግል ስልት ልዩነታቸውን እንደሚተጋገዙ እንጂ እርስ በእርስ እንደሚጣፉ ምርጫዎች አርገው መውሰድ የለባቸውም። ከዚህ ይልቅ ተሰብስበውና ተወያይተው የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አጥቂነት የሚይዙበትን ዘዴ ቢቀይሱ

ለኢህአዴግ አንድ ወጥ የሆነ አመጻኛ የትግል ስልት ሃቀኛና ሁለገብ አጸፋ መስጠት ስለሚችሉ የህዝባችንን የመከራ ዘመን ለማሳጠር ታሪክ የማይረሳው አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይቆጠራል።

# የእብዶች ሎጅክ

የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት አስራ አምስት ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሶስት ጋዜጦች ከህትመት ውጭ እንዲሆኑ ከማድረግ አልፎ በነጻው ፕሬስ ላይ ቀደም ሲልም ተያይዞት የነበረውን የመንግሥታዊ ሽብር ዘመቻ ወደ አዲስ ምእራፍ አሸጋግሮ የጋዜጦችን ጽ/ቤትና ንብረት በእሳት እስከማጋየት ደርሷል።

ወያኔ ወደዚህ አዲስ የሽብር ስልት ለምን እንደተሸጋገረ ብዙ ታዛቢዎች ግራ ተጋብተዋል። ይሁም ሆኖ ከአርብ ማታ ወዲህ ተደጋግመው የሚመጡ ሁለት ምክንያቱች አሉ። በአንድ በኩል የሀገሪቱ ውስጣዊ የፖለቲካና ወታደራዊ ሁኔታ ሲሆን ሌላው ደግሞ በመጋቢት አጋማሽ የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ያደርጋሉ የተባለው ጉብኝት ጋር ያያይዙታል። እነዚህ ምክንያቶች በርግጥም እውነት ከሆኑ የወያኔ መሪዎች የተከተሉት የእብዶች ሎጅክ ነው ማለት ይቻላል።

የሃገሪቱን ውስጣዊ ሁኔታ ምክንያትነት እንመልከት። ርግጥ ዛሬ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ እየሆነ የመጣው በአንድ በኩል በወያኔ በራሱ ውስጥ ያለው ቅራኔና በሌላ በኩል ደግሞ ከእለት እለት እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለው ጸረ ወያኔ የሆነው የተቃዋሚ ኃይሎች ሁለገብ ትግል አለ። ይህ እንደምክንያት ከተወሰደ በእርግጥም ህዝቡ ከሚጠረጥረውና ታዛቢዎች ከሚተነትኑት በላይ ሁኔታው አንዳንድ የወያኔ መሪዎች የሚይዙት የሚለቁት አሳጥቷቸዋል ማለት ነው። ነገር ግን ደግሞ ከዚህ ውጥረት ሽብርን በመፍጠር እንወጣለን ካሉ እነዚህ የወያኔ መሪዎች የሚከተሉት የእብዶች ሎጅክ ነው ከማለት ሌላ ምንም መጨመር አይቻልም። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በወያኔ በራሱ ውስጥ የአጥፍቶ መጥፋት ፖሊስን በሚከተሉና ለሃገሪቱ ችግሮች ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስቀድሙ መፍትሄዎችን በሚሹት ኃይሎች መሃከል ያለውን ቅራኔ ያባብሰዋል እንጂ አያረግበውም። በጸረ ወያኔ ትግል በተሰማሩት ኃየሎችም አካባቢ የሚደረገውን ሁለገብ ትግል ይበልጥ የሞት ሽረት ተጋድሎ መልክ እየሰጠ ያጎለብተዋል እንጂ በምንም ዓይነት አያበርደውም።

ሁለተኛው የሚሰነዘረው ምክንያት የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ያደርጋሉ ከተባለው ጉብኝት ጋር የተያያዘ ነው። እንደነዚህ ታዛቢዎች ከሆነ የወያኔ አንዳንድ መሪች ዓላማ አቅፋ ድግፋ የያዘቻቸው የአሜሪካ መሪ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ቢያንስ በአዲስ አበባ ደረጃ ከተቃዋሚ የጸዳችና ነጻው ፕሬስ ህዝቡን መቀስቀስ የማይችልባት የተረጋጋች የምትመስል አገር ለማሳየት ይፈልጋሉ።

እንዲህ ዓይነቱ ሎጅክ ደግሞ ከእብደትም እብደት ነው።

መጀመሪያ አንድ ጨርሶ እንግዳ የሚሆን ነገር አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የነጻ ፕሬስ፣ የዲሞክራሲ፣ የሰው ልጅ መብት ግንባር ቀደም ተሟጋች ነኝ የምትል አገር መሪ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ባይሆን በጎደለ እንዲሟላ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል እንጂ ለሳቸው እጅ መንሻ ሲባል ይህ መከረኛ ህዝብ ከወትሮው ይበልጥ የሚንገላታበት፣ ድሮውንም በሞት